

# ለአረጋውያንና አካል ጉዳተኞች የሽፋን አማራጮች

Apple Health (Medicaid) ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ፣ ማየት የተሳናቸው ወይም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ወይም የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች (LTSS) ለሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች ሽፋን ይሰጣል።

## የሽመገሉ፣ ማየት የተሳናቸው ወይም አካል ጉዳተኞች (ABD)

ዕድሜዎ 65 እና ከዚያ በላይ፣ ማየት የተሳናቸው ወይም የአካል ጉዳተኛ ከሆኑና የገቢና የንብረት መስፈርቶችን ካሟሉ፣ ዋሽንግተን Apple Health (Medicaid) የጤና እንክብካቤ ሽፋን ሊሰጥና ለሜዲኬር ፕሪሚየምና የህክምና ወጪዎችን ለመክፈል ሊረዳ ይችላል።

ሆስፒስን ጨምሮ ስለ ሽፋን አማራጮች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **hca.wa.gov/free-or-low-cost-health-care/i-need-medical-dental-or-vision-care/long-term-care-and-hospice** ይጎብኙ።

## ለABD ሽፋን ማመልከት

- **ኦንላይን: washingtonconnection.org**ን ይጎብኙ
- **የወረቀት ማመልከቻ:** ቅጽ 18-005 ያትሙ፣ በ **hca.wa.gov/classic-health-care-application** ላይ ይገኛል።
  - **ፖስታ ፦** DSHS Community Services Division, P.O. Box 11699, Tacoma, WA 98411-6699.
- **በአካል፦** በአጠገብዎ ያለውን የማህበረሰብ አገልግሎት ቢሮ ይጎብኙ። **dshs.wa.gov/office-locations**ን ይጎብኙ።
- ለጥያቄዎች የDSHS ደንበኛ አገልግሎትን በዚህ ላይ ይደውሉ 1-877-501-2233.

## የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች (LTSS)

በግምገማ መሰረት የተወሰኑ መመዘኛዎችን ካሟሉ Apple Health ለቤትዎ አገልግሎት፣ ለማህበረሰብ መኖሪያ እንክብካቤ ተቋም፣ ለታገዘ የመኖሪያ ተቋም፣ ለአዋቂ ቤተሰብ ቤት ወይም ለነርሲንግ ተቋም ይከፍላል።

ለሽማግሌዎች የተዘጋጀ ድጋፍ (TSOA)ና ሜዲኬድ አማራጭ እንክብካቤ (MAC) በአሁኑ ጊዜ ጓደኛን ወይም የቤተሰብ አባልን ያለምንም ወጪ የሚንከባከቡ ተንከባካቢዎችን የሚረዱ የLTSS ፕሮግራሞች ናቸው።

## ለLTSS በማመልከት ላይ

- **ኦንላይን: washingtonconnection.org** ን ይጎብኙ
- **የወረቀት ማመልከቻ:** ቅጽ 18-005 ያትሙ፣ በ **hca.wa.gov/classic-health-care-application** ይገኛል።
- **በአካል፦** በአጠገብዎ የሚገኝ የቤትና የማህበረሰብ አገልግሎት ቢሮን ይጎብኙ። **dshs.wa.gov/office-locations**ን ይጎብኙ።
- ለጥያቄዎች በአካባቢዎ የሚገኘውን የቤትና የማህበረሰብ አገልግሎት ቢሮ ይደውሉ። **dshs.wa.gov/office-locations**ን ይጎብኙ።

**ማስታወሻ:** ለእነዚህ ፕሮግራሞች የገቢና የሁብት መስፈርቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

Washington Apple Health

Washington State Health Care Authority

HCA 19-032 AM (9/23) Amharic

## የመናገር ወይም የመስማት ችግር ፣ ወይም የመንቀሳቀስ ጉዳዮች

የንግግር ወይም የመስማት ችግር ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ካለብዎ ቀጠሮ ሲይዙ ለእንግዳ ተቀባይዋ መንገር አለብዎት። የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ እንግዳ ተቀባይ ማንኛውንም አስፈላጊ ዝግጅት ለማድረግ ይረዳዎታል።

## የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

እንግሊዝኛ በደንብ የማይናገሩ ከሆነ ወይ መስማት የማችሉ ከሆነ፣ መስማት የተሳነውና ዓይነ ስውር ወይ የመስማት ችግር ካለብዎት ፕሮፌሽናል አስተርጓሚዎች በብዙ ቋንቋዎች የምልክት ቋንቋዎችን ጨምሮ በነፃ አገልግሎት ይሰጥዋታል። ቀጠሮዎን ሲይዙ አስተርጓሚ እንደሚፈልጉ ለእንግዳ ተቀባይዋ ያሳውቁ። ለተጨማሪ መረጃ **hca.wa.gov/interpreter-services** ይጎብኙ።

## የትራንስፖርት አገልግሎቶች

ወደቀጠሮዎት ሊሄዱ የሚችሉበት አማራጭ ከሌሎት መጓጓዣ ለማግኘት ይፈድሎታል። ቀጠሮው በ Apple Health አገልግሎት ሽፋን ማግኘት አለበት። በአካባቢዎ መጓጓዣን ወይም ሀኪም ለመፈለግ እርዳታ ከፈለጉ እባክዎ በስልክ ቁጥር 1-800-562-3022 ይደውሉ። ለተጨማሪ መረጃ **hca.wa.gov/transportation-help** ይጎብኙ።

HCA ሁሉንም የሚተገበሩ የፌደራል እና የ Washington ግዛት የሰብአዊ መብት ህጎችን ያከብራል እንዲሁም ለምንሰጠው አገልግሎቶች እኩል ተደራሽነትን ያረጋግጣል። የመኖሪያ ሁኔታ ካስፈለገዎት ወይም ሰነዶችን በሌላ ቋንቋ ወይም ቅርጽ ማግኘት ከፈለጉ እባክዎ በ1-800-562-3022 (TRS: 711) ይደውሉ።

